**ስለሆነም**

**ሀ/ የሲዳማ ሕዝብ**

1ኛ/ በተፈጠረው እክል ተስፋ ባለመቁረጥ በሀገርና ከሀገር ውጭ ያሉ የሲዳማ ድርጅቶች ለአንድ አላማ በአንድነት እንድሰሩ ከፍተኛ ጫናና ግፍት እንድያደርግ ለሁሉም የብሔሩ ዜጋ ኃላፍነት እንዳለበት እናሳስባለን::

2ኛ/ የእያንዳንዱ ድርጅት ገጽታ ከሞላ ጎደል ከላይ የተቀመጠ እውነታ መሆኑን በመረዳትና የበለጠም በማረጋገጥ የማናቸውም ድርጅት አባልና ደጋፍ ከመሆኑ በፍት እያንዳንዱ ዜጋ የበኩሉን ጥናትና ጥንቃቄ በማድረግ ከማንኛውም ወገንተ"ነትና ጎሰ "ነት በፀዳ መልኩ የሲዳማን ብሔራዊ ጥቅም በማስቀደም የግሉ ውሳኔ ላይ እንድደርስ አደራ እንላለን::

3ኛ/ በማንም የፖለቲካ ድርጅት አነሳሽነትና ደጋፍነት ሳይሆን በዘመናት ግፍና ብሶት ያቀጣጠልከውን የውሳኔዬ ይከበር ተቃውሞህንና ትግልህን በሰላማዊ መንገድ ከበፍቱ አጠናክረህ እንድትቀጥል እናሳስባለን::

4ኛ/ የነፃነትና የዲሞክራሲ ታጋይ ድርጅቶች የፀረ ወያኔ ትግላቸውን ለማስተባበር በኔዘርላንድ ያቋቋሙት የነፃነት; የዲሞክራሲና የፍትሕ የጋራ ግንባር አላማ መሳካት በግልም ሆነ በጋራ የበኩላችሁን አስተዋጽኦ እንድታበረክቱ ጥሪ እናቀርባለን::

**ለ/ ለአጋር ድርጅቶችና ወገኖች**

1ኛ/ የሲዳማ መጠናከር የጋራ አላማችን የሆነው የፀረ ወያኔ ትግልን ለማሳካት የሁላችን ጥንካሬ መሆኑን በመገንዘብ የሲዳማ ድርጅቶች በጋራ ለመንቀሳቀስ የጀመሩት ውይይት ለምን እንደተቋረጠ ሐቁን በማጤን የአንድነት አላማው መሳካት የበኩላችሁን ጫና እንድታደርጉ እንጠይቃለን::

2ኛ/ SLF እስካሁን ከተለያዩ ወገኖች ከሚያገኘው ድጋፍ አንፃር ምን ያህል ድርጅታዊ ብቃትና ጥንካሬ እንዳለውና የሚያገኘውን ድጋፍ በትክክል ለታለመለት የሕዝብ ትግል በአግባቡ እያዋለ መሆን አለመሆኑን በመገምገም ለወደፍቱም የሚሰጠው ድጋፍ ለግለሰቦች ሳይሆን ለሕዝባዊ ትግል አላማ እንድውል ሆኖ የድርጅቱን ውስጣዊ መዋቅሩን; የአመራር ብቃቱን; በግልጸ"ነትና በተጠያቂነት አሰራር የሚጠናከርበት ስልት አስፈላጊ መሆኑን በመጠቆም ድርጅቱ በሀገር ቤት ከሚታየው የሲዳማ ሕዝብ ፀረ ወያኔ ትግል አንፃር ምን ያህል የሕዝቡን ትግል እያስተባበረ እንዳለና እስካሁንም ለምን የአንድና የሁለት ግለሰቦች ብቻ ሆኖ እንደቀረ ከግንዛቤ ውስጥ በማስገባት አማራጭ አካሄድ እንድኖር አጋር ድርጅቶቹ እንድያስቡበት አበክረን እንጠይቃለን::

***ድል ለነፃነትና ዲሞክራሲ ፈላጊ ታጋዮች !***